የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ ዓመት ቁጥር ፴፬
አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No. 34
ADDIS ABABA, 10th July, 2024

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፰/፪ሺ፲፮

ለኢነርጂ ዘርፍ የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ………………………………. ገጽ ፲፭ሺ፮፻፲፯

**Content**

Proclamation No. 1318/2024

Italian Republic Loan Agreement for financing Budget Support Programme dedicated to Ethiopian Energy Sector Ratification Proclamation..……………………....Page 15617

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፰/፪ሺ፲፮**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን መንግሥት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለኢነርጂ ዘርፍ የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ፹፫ ሚሊዮን ፭፻ሺ ዩሮ (ሰማንያ ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ዩሮ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ጥር ፳፱ ቀን ፳ሺ፲፮ ዓ.ም የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህን ስምምነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፭ ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም ባኣካሄደዉ ፲፯ኛ መደበኛ ስብሰባ ያጸደቀዉ በመሆኑ፤

**PROCLAMATION NO.** 1318/2024

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ITALIAN REPUBLIC**

**WHEREAS**, the Loan Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic stipulating that the Government of the Italian Republic shall provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to 83,500,000 Euro (Eighty Three Million five hundred thousand Euro) for financing Budget Support Programme dedicated to Ethiopian Energy Sector was signed on the 7th day of February 2024;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Loan Agreement at its 17th regular session, held on the 14th day of March 2024;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለኢነርጂ ዘርፍ የበጀት ድጋፍ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፲፰/፪ሺ፲፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መጽደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል ጥር ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ..ም የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር F.ROT/AID 23/006/00 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፹፫ ሚሊዮን ፭፻ሺ ዩሮ (ሰማንያ ሶስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ዩሮ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፫ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**NOW, THERFORE**, in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Italian Republic Loan Agreement for financing Budget Support Programme dedicated to Ethiopian Energy Sector Ratification Proclamation No. 1318/2024".

**2. Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement Number F.ROT/AID 23/006/00 signed on the 7th day of February, 2024 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Italian Republic is hereby ratified.

**3. Power of the Ministry of Finance**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an equivalent to 83,500,000 Euro (Eighty Three Million five hundred thousand Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force upon its publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, On this 10th Day of July, 2024**

**SAHLE-WORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**